፩ ፤ አኰቴተ ፡ ቍርባን ፡ ዘቅዱስ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘደሴተ ፡ ቆጵሮስ ። ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ **ምስለ ፡ ኵልክሙ ።**

ይ ፡ ሕ ፡ **ምስለ ፡ መንፈስከ ።**

ይ ፡ ካ ፡ **አእኵትዎ ፡ ለአምላክነ ።**

ይ ፡ ሕ ፡ **ርቱዕ ፡ ይደሉ ።**

፩ ፤ የቆጵሮስ ፡ ደሴት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ የተናገረው ፡ የቍርባን ፡ ምስጋና ። ጸሎቱና ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ **ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ።**

ይ ፡ ሕ ፡ **ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።**

ይ ፡ ካ ፡ **አምላካችንን ፡ አመስግኑት ።**

ይ ፡ ሕ ፡ **ዕውነት ፡ ነው ፡ ይገባል ።**

ይ፡ ካ፡ አልዕሉ ፡ አልባቢክሙ ።
ይ፡ ሕ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አም
ላክነ ።

፫ ፤ ይ፡ ካ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በዕበዩ ፡ ቅዱስ ፡ በቅዳሴሁ ፤ እኩት ፡
በአኰቴቱ ፤ ወስቡሕ ፡ በስብሓቲሁ ።
ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይብልዎ ፡ እማ
እዜ ፤ ወማእከላዊ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይብልዎ ፡
እስከ ፡ ይእዜ ፡ ወደኃራዊ ፡ ውእቱ ፡ ዘአይ
ብልዎ ፡ እስከ ፡ ዝየ ።

፬ ፤ አልቦ ፡ ጥንት ፡ ለህላዌሁ ፤ ወአልቦ ፡
ማኅለቅት ፡ ለክዋኔሁ ፤ አልቦ ፡ ኍልቍ ፡
ለመዋዕሊሁ ፤ ወአልቦ ፡ ሐሳብ ፡ ለዓመታ
ቲሁ ። ወአልቦ ፡ ርስዓን ፡ ለውርዛዌሁ ፤
ወአልቦ ፡ ድካም ፡ ለጽንዐ ፡ ኃይሉ ፤ ወአ
ልቦ ፡ ሙስና ፡ ለመልክኡ ፤ ወአልቦ ፡ ጽል
መት ፡ ለብርሃነ ፡ ገጹ ።

፭ ፤ አልቦ ፡ ድንጋግ ፡ ለባሕረ ፡ ጥበቡ ፤
ወአልቦ ፡ መስፈርት ፡ ለሣህለ ፡ ትእዛዙ ፤
አልቦ ፡ ዐቅም ፡ ለስፍሐ ፡ መንግሥቱ ፤ ወአ
ልቦ ፡ ወሰን ፡ ለራኅበ ፡ ምዅናኑ ።

፮ ፤ ሥውር ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይረክብዎ ፡
በኅሊና ፡ ወምጡቅ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይጤይ
ቅዎ ፡ በልቡና ፤ ነዋኅ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይበጽ
ሕዎ ፡ አንስርት ፤ ቀላይ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይዐ
ብትዎ ፡ ዓሣት ።

፯ ፤ ልዑል ፡ ውእቱ ፡ እምአርእስተ ፡ አድ
ባር ፤ ወዕሙቅ ፡ ውእቱ ፡ እምዕመቀ ፡
ባሕር ። ዕኑዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይትናሥእዎ ፡
ነገሥት ፤ መዋዒ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይትቃወ
ምዎ ፡ መኳንንት ።

፰ ፤ ጠቢብ ፡ ውእቱ ፡ ዘያኀጕል ፡ ምክረ ፡
ጠቢባን ፤ ማዕምር ፡ ውእቱ ፡ ዘያረስዕ ፡
ኅሊና ፡ መካርያን ፡ ኃያል ፡ ውእቱ ፡ ዘይ
ፈትሕ ፡ ልጓማተ ፡ ጽኑዓን ፤ ተባዕ ፡ ውእቱ ፡
ዘያደቅቅ ፡ አስናነ ፡ ኃጥአን ፡ ወይቀጠቅጥ ፡
መዝራዕተ ፡ ዕቡያን ።

፱ ፤ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ዘያነሥር ፡ ገጸ ፡
መደልዋን ፡ ክሁሊ ፡ ውእቱ ፡ ዘያአትት ፡
ብርሃነ ፡ ረሲዓን ።

ይ፡ ካ፡ ልቡናችሁን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድ
ርጉ ።
ይ፡ ሕ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡ አለን ።

፫ ፤ ይ፡ ካ፡ እግዚአብሔር ፡ በገናንነቱ ፡
ገናና ፡ ነው ፤ በቅድስናው ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ፤
በምስጋናው ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፤ በክብ
ሩም ፡ የከበረ ፡ ነው ።
ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ የማይሉት ፡ ቀዳማዊ ፡
ነው ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የማይሉት ፡ ማእከላዊ ፡
ነው ፤ እስከዚህ ፡ የማይሉትም ፡ ደኃራዊ ፡
ነው ።

፬ ፤ ለአነዋወሩ ፡ ጥንት ፡ የለውም ፤ ለአ
ኳኋኑም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፤ ለዘመኑ ፡
ቍጥር ፡ የለውም ፤ ለዓመታቱም ፡ ልክ ፡
ቍጥር ፡ የለውም ፤ ለውርዝውናው ፡ ማር
ጀት ፡ የለበትም ፤ ለኃይሉም ፡ ጽናት ፡
ድካም ፡ የለበትም ፤ ለመልኩ ፡ ጥፋት ፡ የለበ
ትም። ለፊቱ ፡ ብርሃንም ፡ ጨለማ፡የለበትም።

፭ ፤ ለጥበቡ ፡ ባሕር ፡ ድንበር ፡ የለውም ፡
ለቸእዛዙም ፡ ይቅርታ ፡ መስፈርት ፡ የለ
ውም፤ለመንግሥቱ፡ስፋት ፡ ዐቅም ፡ ልክ ፡
የለውም ፤ ለአገዛዙም ፡ ስፋት ፡ ወሰን ፡
የለውም ።

፮ ፤ በኅሊና ፡ የማያገኙት ፡ ሥውር ፡ ነው ፤
በልቡናም ፡ የማይረዱት ፡ ምጡቅ ፡ ነው ፤
አንሥርት ፡ የማይደርሱበት ፡ ረጅም ፡ ነው ፤
ዓሣዎች ፡ የማይዋኙበት ፡ ጥልቅ ፡ ነው ።

፯ ፤ ከተራሮች ፡ ራስ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ነው ፤ ከባሕር ፡ ጥልቅነት ፡ ይልቅ ፡ ጥልቅ ፡
ነው ፤ ነገሥታት ፡ የማይነሣሡበት ፡ ጽኑ ፡
ነው ፤ መኳንንት ፡ የማይቃወሙት ፡ አሸ
ናፊ ፡ ነው ።

፰ ፤ የጥበበኞችን ፡ ምክር ፡ የሚያጠፋ ፡
ጥበበኛ ፡ ነው ፤ የሚመክሩትን ፡ ሰዎች ፡
አሳባቸውን ፡ የሚያስረሳ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤
የጸኑ ፡ ልጓሞችን ፡ የሚፈታ ፡ ኃያል ፡ ነው ፤
የኃጥአንን ፡ ጥርሶች ፡ የሚያደቅ ፤ የትዕቢ
ተኞችንም ፡ ክንድ ፡ የሚቀጠቅጥ ፡ ብርቱ ፡
ነው ።

፱ ፤ የግብዞችን ፡ ፊት ፡ የሚያዋርድ ፡
ክቡር ፡ ነው ። የዝንጉዎችን ፡ ብርሃን ፡ የሚ
ያርቅ ፡ ከሃሊ ፡ ነው ።

፲ ፤ ዋሕድ ፡ ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ቢጽ ፡ ወብሑት ፡ ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ አዝማድ ። ይትኃጐላ ፡ ሰማያት ፡ ወትማስን ፡ የብስ ፤ ወኵሉ ፡ ይበሊ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ውእቱሰ ፡ ውእቱ ፡ ክመ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

፲፩ ፤ መንክር ፡ ውእቱ ፡ ተሳህያ ፡ ለባሕር ፡ መንክርሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ በአርያሙ ። አልቦ ፡ ዘይመስሎ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይትዔረዮ ፡ እምኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወእምኵሉ ፡ ደቂቀ ፡ አማልክት ፡ ባሕቲቱ ፡ አምላክ ፡ ወባሕቲቱ ፡ እግዚእ ፡ ባሕቲቱ ፡ ፈጣሪ ፡ ወባሕቲቱ ፡ ገባሪ ።

፲፪ ፤ ኢየኀሥሥ ፡ መርድአ ፡ በእንተ ፡ ኪን ፡ ዘሐለየ ፡ ወኢይፈቅድ ፡ መምክረ ፡ በእንተ ፡ ምግባር ፡ ዘፈተወ ። የአምር ፡ ኵሎ ፡ እምቅድመ ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ ዘኮነ ፡ ቅድመ ፡ ወዘኢተገብረ ፡ ከመ ፡ ዘተገብረ ።

፲፫ ፤ የሐትት ፡ ኅሊና ፡ እንዘ ፡ ኢይሴአል ወይፈትን ፡ አልባበ ፡ እንዘ ፡ ኢየኀሥሥ ፤ ወይሬኢ ፡ ዘውስተ ፡ ጽልመት ፡ ዘእንበለ ፡ ማኅቶት ።

፲፬ ፤ ወየአምሮ ፡ ለጻድቅ ፡ እንበለ ፡ ይግበር ፡ ጽድቀ ፤ ወይቤይኖ ፡ ለኃጥእ ፡ እንበለ ፡ ይግበር ፡ ኃጢአተ ፤ ይሌብዎሙ ፡ ለልቡባን እንበለ ፡ ይፃኡ ፡ እምሐቌ ፡ አቡሆሙ ፤ ወይጤይቆሙ ፡ ለኃጥአን ፡ እምከርሠ ፡ እሞሙ ።

፲፭ ፤ አልቦ ፡ ዘይትኔብአ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይሜወሮ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይትከበት ፡ እምኔሁ ፡ ኵሉ ፡ ክሡት ፡ በኀቤሁ ፡ ወኵሉ ፡ ስጡሕ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ኵሉ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፉ ወኵሉ ፡ ጽውዕ በኅሊናሁ ።

፲፮ ፤ ይገብር ፡ ዐቢያተ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቈ ክቡራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ዘአልቦ ፡ ዐሠር ፡ ዕፁብ ፡ ግብሩ ፡ እምዘርኢነ ፤ ወመንክር ፡ ኃይሉ ፡ እምዘሰማዕነ ፤ ወመድምም ፡ ስብሓቲሁ ፡ እምዘነገሩነ ።

፲፯ ፤ ውእቱ ፡ ገብረ ፡ ብርሃነ ፡ እምጽልመት ፡ ወየአምር ፡ ፈሊጦቶ ፡ ለደመና ፡ ይከፍሎ ፡ ለማይ ፡ ዘከመ ፡ ፈቀደ ፡ ወይሜውር ፡ ኅሩያነ ፡ በደመና ።

፲ ፤ ባልንጀራ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ዘመድ ፡ የሌለው ፡ ሥሉጥ ፡ ነው ፤ ሰማያት ፡ ይጠፋሉ ፤ የብስም ፡ ትጠፋለች ፤ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃል ። እርሱ ፡ ግን ፡ እስከ ዘለዓለሙ ፡ እርሱ ፡ ነው ።

፲፩ ፤ የባሕር ፡ መመላለስዋ ፡ ድንቅ ፡ ነው ድንቅስ ፡ በልዕልናው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ የሚመስለው ፡ የለም ፤ ከፍጥረትም ፡ ሁሉ ፡ ከአልማክትም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ የሚተካከለው ፡ የለም ። እርሱ ፡ ብቻ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ብቻ ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ ፈጣሪም ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ሠሪም ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፲፪ ፤ ስላሰበው ፡ ጥበብ ፡ ረዳት ፡ አይሻም ፡ ስለ ፡ ወደደውም ፡ ሥራ ፡ መካር ፡ አይሻም ። ሳይሆን ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አድርጎ ፤ ያልተደረገውንም ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ አድርጎ ፡ ሁሉን ፡ ያውቃል ።

፲፫ ፤ ሳይጠይቅ ፡ ኅሊናን ፡ ይመረምራል ፤ ሳይመረምር ፡ ልቡናን ፡ ይፈትናል ፤ ያለ ፡ መብራት ፡ በጨለማ ፡ ያለውን ፡ ያያል ።

፲፬ ፤ ጻድቁን ፡ ጽድቅን ፡ ሳይሠራ ፡ ያውቀዋል ፤ ኃጥኡንም ፡ ኃጢአት ፡ ሳይሠራ ፡ ያውቀዋል ፤ ልበኞችን ፡ ከአባታቸው ፡ ወገብ ፡ (አብራክ ፡) ሳይወጡ ፡ ያውቃቸዋል ፤ ኃጥአንንም ፡ ከእናታቸው ፡ ማኅፀን ፡ ያውቃቸዋል ።

፲፭ ፤ የሚሸሸገው ፡ የለም ፤ የሚሠወረውም ፡ የለም ፤ ከርሱም ፡ የሚሠወር ፡ የለም ፤ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተገለጸ ፡ ነው ፤ በዓይኖቹም ፡ ፊት ፡ ሁሉ ፡ የተዘረጋ ፡ ነው። ሁሉ ፡ በመጽሐፉ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፤ በኅሊናውም ፡ ሁሉ ፡ የተጠራ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ታላላቆችን ፡ መመርመር ፡ የሌለባቸውን ፡ የተደነቁ ፡ የከበሩ ፡ ሥራዎችን ፡ ይሠራል ። ሥራው ፡ ከአየነው ፡ ይልቅ ፡ ዕፁብ ፡ ነው ፤ ኃይሉም ፡ ከሰማነው ፡ ይልቅ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ ጌትነቱም ፡ ከነገሩን ፡ ይልቅ ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

፲፯ ፤ ከጨለማ ፡ ለይቶ ፡ ብርሃንን ፡ ፈጠረ ደመናውን ፡ መለየት ፡ ያውቃል ። ውኃውን እንደ ፡ ወደደ ፡ ይከፍለዋል ፤ የተመረጡትን ፡ በደመና ፡ ይሠውራል ።

፲፰ ፤ ሣረራ ፡ ለምድር ፤ ወሠርዐ ፡ አምጣኒሃ ፤ ወተከለ ፡ ከመ ፡ ወኢምንት ፡ ሕላቃቲሃ ፡ ወአስተኀደረ ፡ መዓዝኒሃ ።

፲፱ ፤ ሐፀራ ፡ ለባሕር ፡ በአናቅጽ ፡ አመ፡ ወፅአት ፡ እምከርሠ ፡ እማ ፤ ወረሰየ ፡ ላቲ ፡ ደመና ፡ ልብሳ ፤ ወበጊሜ ፡ ጠብለላ ። ወገብረ ፡ ላቲ ፡ ወሰነ ፤ ወሜመ ፡ ውስቴታ ፡ መዓፁተ ፡ ወመናግሥተ ፡ ወይቤላ ፡ እስከ፡ ዝየ ፡ ብጽሒ ፡ ወኢትትዐደዊ ፡ እምወሰንኪ ፤ ዳእሙ ፡ ይትከወስ ፡ ማዕበልኪ ፡ በውስቴትኪ ።

፳ ፤ ወበላዕሌሃ ፡ ተሠርዐ ፡ ኀሓ ፡ ጽባሕ ፤ ወኮከበ ፡ ጽባሕኒ ፡ አእመረ ፡ ትእዛዞ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ፅቡረ ፡ እምድር ፡ ወፈጠረ ፡ ዘሕያው ፡ ወረሰዮ ፡ ይትናገር ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

፳፩ ፡ ውእቱ ፡ በጽሐ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ባሕር ፡ ወአንሶሰወ ፡ ውስተ ፡ ዐሠረ ፡ ቀላይ ።

፳፪ ፤ ሎቱ ፡ ይትረኀዉ ፡ አናቅጸ ፡ ሞት፡ እምግርማሁ ፡ ወአጸውተ ፡ ሲኦል ፡ ይደነግፁ ፡ እምከመ ፡ ርእይዎ ። ውእቱ ፡ የአምር፡ ራኀበ ፡ ዘታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ወዘይከውን ፡ በመልዕልተ ፡ ሰማይ ።

፳፫ ፡ ወበትእዛዙ ፡ ይወፅእ ፡ ሐመዳ ፡ እመዝገቡ ፡ ወይትመየጥ ፡ አዜብ ፡ ዘታሕተ ፡ ሰማይ ። ያጸንዖ ፡ ለዝናም ፡ በፍኖተ ፡ በድው ፡ ከመ ፡ ይዝንም ፡ ብሔረ ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ሰብእ ፡ ወኢይነብሮ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፳፬ ፤ ውእቱ ፡ ዐቀመ ፡ ሙሐዘ ፡ ማይ ፡ ወያርኆ ፡ ክረምተ ፡ በበዓመት ፡ ወያመጽእ ፡ ለሐጋይ ፡ ድኅረ ፡ በዕድሜሁ ። ውእቱ ፡ ይጼውዖ ፡ ለደመና ፡ በቃሉ ፡ ወያወሥእ ፡ ማይ ፡ እንዘ ፡ ይርዕድ ።

፳፭ ፤ ውእቱ ፡ ይፌንዎ ፡ ለፀዓዕ ፡ ወየሐውር ፡ ወይሠጠዎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ምንት ፡ ውእቱ ። ውእቱ ፡ ይኄልቆ ፡ ለደመና ፡ በጥበቡ ፡ ወያጸንኖ ፡ ለሰማይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

፳፮ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ለብሰ ፡ ኃይለ ፡ አርያም ፡ ወተረሰየ ፡ በስብሐት ፡ ወበክብር ።

፳፯ ፡ ኪያሁ ፡ ይቄድሱ ፡ ኪሩቤል ፡ እሳታውያን ፡ ወሱራፌል ፡ ልቡሳነ ፡ ብርሃን ፡ በቃል ፡ ዘኢየዐርፍ ፡ ወበአፍ ፡ ዘኢያረምም

፲፰ ፤ ምድርን ፡ ፈጠራት ፡ መጠንዋንም ፡ አዘጋጀ ፤ ፍጻሜዋንም ፡ እንደምንም ፡ ተከለ ማዕዘንዋንም ፡ አጸና ።

፲፱ ፤ ባሕርን ፡ ከእናትዋ ፡ ሆድ ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ በበሮች ፡ አጠራት ። ልብሷንም ፡ ደመና ፡ አደረገላት ፤ በጉም ፡ ጠቀለላት ፤ ወሰን ፡ አደረገላት ፤ በውስጥዋም ፡ መዝጊያዎችንና ፡ ቊልፎችን ፡ አደረገላት ። እስከዚህ ፡ ድረሺ ፤ ከወሰንሺም ፡ አትተላለፊ ፤ ማዕበልሽ ፡ በውስጥሽ ፡ ይመላለስ ፡ (ይነቃነቅ ፡) እንጂ ፡ አላት ።

፳ ፤ በበላይዋ ፡ ላይ ፡ የንጋት ፡ ብርሃን ፡ ተዘጋጀ ፤ የአጥቢያ ፡ ኮከብም ፡ ትእዛዙን ፡ ዐወቀ ። እርሱ ፡ ከምድር ፡ ጭቃን ፡ ነሥቶ ፡ ሕያው ፡ የሆነውን ፡ ፈጠረ ። በምድርም ፡ ላይ ፡ እንዲነጋገር ፡ አደረገው ።

፳፩ ፡ እርሱ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ደረሰ ። በጥልቅ ፡ ፍለጋም ፡ ተመላለሰ ።

፳፪ ፤ ከግርማው ፡ የተነሣ ፡ የሞት ፡ ደጆች ፡ ይከፈታሉ ፤ የሲኦል ፡ በሮችም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ይደነግጣሉ ። ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ስፋቱን ፤ ከሰማይ ፡ በላይ የሚሆነውንም ፡ እርሱ ፡ ያውቀዋል ።

፳፫ ፤ በርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ዋግ ፡ ከመዝገቡ ፡ ይወጣል ። ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ አዜብ ፡ (ነፋስ ፡) ይመላለሳል ። ዝናምን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያጸናዋል ፡ ሰው ፡ በሌለበትና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በማይኖርበት ፡ ይዘንም ፡ ዘንድ ።

፳፬ ፤ እርሱ ፡ የውሀውን ፡ መፍሰሻ ፡ ወሰነ ፡ ክረምትንም ፡ በየሙቱ ፡ ይከፍታል ፡ በጋውንም ፡ ኋላ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ያመጣዋል ። ደመናውንም ፡ በቃሉ ፡ ይጠራዋል ፤ ውኃም ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ይመልስለታል ።

፳፭ ፤ ብልጭልጭታውን ፡ እርሱ ፡ ይልከዋል ፤ እርሱም ፡ ይሄዳል ፤ ምንድር፡ነው እያለ ፡ ይመልስለታል ። እርሱ ፡ ደመናን፡ በጥበቡ ፡ ይቆጥረዋል ። ሰማይን፡ (ጠፈርን) ወደ ፡ ምድር ፡ ያዘነብለዋል።

፳፮ ፤ እርሱ ፡ ብቻ ፡ የአርያምን ፡ ኃይል፡ ለበሰ ፡ በምስጋናና ፡ በክብር ፡ ተጌጠ።

፳፯ ፡ እሳታውያን ፡ ኪሩቤል ፡ ብርሃን፡ የለበሱ ፡ ሱራፌልም ፡ እርሱን ፡ ያመሰግናሉ ። በማያርፍ ፡ ቃል ፡ ዝም ፡ በማይል፡

ወበልሳን ፡ ዘኢይደክም ። ወይብሉ ፡ ኵሎሙ ኅቢሮሙ ፡ በ፩ዱ ፡ ቃለ ፡ አውሥአ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ።

፳፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ አውሥኡ ።

፳፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ።

፴ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ እግዚአብሔር ፡ እግዚአሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወመልዐ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ።

፴፩ ፤ ኵሉ ፡ እምኔሁ ፡ ወኵሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወኵሉ ፡ ዘዚአሁ ። ሰማይ ፡ ሎቱ ፡ ወሰማየ ፡ ሰማያት ፡ እንቲአሁ ። ራኅበ ፡ አርያም ፡ መንበረ ፡ ክብሩ ፤ ወስፍሐ ፡ ምድር ፡ መከየደ ፡ እገሪሁ ።

፴፪ ፤ ፀሐይ ፡ ዚአሁ ፡ ወወርኅ ፡ ሎቱ ፤ ወከዋክብት ፡ ተግባረ ፡ እደዊሁ ። ደመናት ፡ ሐዋርያቲሁ ፤ ወነፋሳት ፡ ሠረገላቲሁ ፤ ወእሳት ፡ ዐረፍተ ፡ ቤቱ ።

፴፫ ፤ ማይ ፡ ጠፈረ ፡ ቤቱ ፤ ሰሌዳ ፡ በረድ ፡ ጸፍጸፈ ፡ ዐውዱ ፤ ወብርሃናት ፡ ደባትሪሁ ፤ ወመብረቅ ፡ ስብሐት ፡ መንጦላዕተ ፡ ምሥዋራቲሁ ፡ ወውስተ ፡ አየራት ፡ ነሶሳዉ ።

፴፬ ፤ ዘበፀዐዕ ፡ ድምፀ ፡ ንባቡ ፤ ቃለ ፡ ነጐድጓዱ ፡ በሠረገላት ፤ ባሕር ፡ ዓመቱ ፤ ወሐይዝተ ፡ አፍላግ ፡ ቅኑያቲሁ ፤ ቀኖር ፡ ወአስሐትያ ፡ ገባርያኑ ፡ ሥምረቱ ።

፴፭ ፤ ያዐርግ ፡ ደመናተ ፡ ለምአጽናፈ ፡ ምድር ። ወገብረ ፡ መብረቀ ፡ ለጊዜ ፡ ዝናም ወይከዑ ፡ ዝናማተ ፡ ከመ ፡ ነጠብጣበ ፡ ማሕየብ ፡ ይዘርዎ ፡ ለጊሜ ፡ ከመ ፡ ሐመድ ፤ ወያወርድ ፡ በረደ ፡ ከመ ፡ ፍተታት ፤ ወያሕመለምል ፡ ሣዕረ ፡ ለእንስሳ ።

በማይደክምም ፡ አንደበት ፡ ሁሉም ፡ ተባብረው ፡ ተሰጥዎ ፡ ባለበት ፡ ባንድ ፡ ቃል፡ የጌትነትህ ፡ ምስጋና ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡ የመላ ፡ ፍጹም ፡ አሸናፊ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር፡ ይላሉ ።

፳፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ተሰጥዎውን ፡ መልሱ ።

፳፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹም ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር፡ የጌትነትህ ፡ ምስጋና ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡የመላ ነው ።

፴ ፤ ይ ፡ ካ ፡ የቅዱሳን ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ነህ ፤ የጌትነትህም፡ምስጋና፡በሰማይና፡ በምድር ፡ መላ።

፴፩ ፤ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ነው ፤ ሁሉም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ ሁሉም ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ ሰማይ በርሱ ፡ ነው ፤ ከሰማያት ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይም ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ የአርያም ፡ ስፋት ፡ የክብሩ ፡ ዙፋን ፡ ነው ፤ የምድርም ፡ ስፋት የእግሩ ፡ መመላለሻ ፡ ናት ።

፴፪ ፤ ፀሐይ ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ ጨረቃም ፡ ከርሱ ፡ ነው ፤ ከዋክብትም ፡ የእጁ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፡ ደመናት ፡ መልክተኞቹ ፡ ነፋሳትም ሠረገላዎቹ ፡ ናቸው ። እሳትም ፡ የቤቱ ፡ ግርግዳ ፡ ነው ።

፴፫ ፤ የቤቱ ፡ ጠፈር ፡ ውኃ ፡ ነው ፤ የዙሪያውም ፡ ጸፍጸፍ ፡ የበረድ ፡ ሰሌዳ ፡ ነው ፤ ድንኳኖቹ ፡ ብርሃናት ፡ ናቸው ። የመሠወሪያ ፡ መጋረጃውም ፡ የብርሃን ፡ መብረቅ ፡ ነው ። መመላለሻውም ፡ በአየር ፡ ነው ።

፴፬ ፤ የመናገሩ ፡ ድምፅ ፡ በብልጭልጭታ ፡ ያለ ፡ ነው ። የነጐድጓድ ፡ ቃል ፡ በሠረገላዎች ፡ አለ ። ባሕር ፡ ባሪያው ፡ ናት የወንዝ ፡ ፈሳሾች ፡ ተገዦቹ ፡ ናቸው ። ቀኖር አስሐትያም ፡ ፈቃዱን ፡ የሚሠሩ ፡ ናቸው ።

፴፭ ፤ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ደመናውን ፡ ያወጣል ፤ መብረቅንም ፡ በዝናም ፡ ጊዜ ፡ አደረገ ፡ ዝናምንም ፡ እንደ ፡ መሽረብ ፡ ነጠብጣብ ፡ ያፈሳል ፤ ጉምን ፡ እንደ ፡ አመድ ፡ ይበትነዋል ፡ በረድንም ፡ እያጠቃቀነ ፡ ያወርዳል ፤ ለእንስሳም ፡ ሣሩን ፡ ያለመልማል ።

፴፮ ፡ ይገብር ፡ በከመ ፡ ሐለየ ፡ ወይፌጽም ፡ በከመ ፡ ወጠነ ፡ ወያጠዐጥዕ ፡ በከመ ፈቀደ ፡ ያሐስም ፡ ወያሴኒ ፡ ያነዲ ፡ ወያብዕል ፡ ያኅሥር ፡ ወያከብር ፡ ይቀትል ፡ ወያሐዩ ፡ ያደዊ ፡ ወይፌውስ ፡ ይኴንን ፡ ወያጸድቅ ።

፴፯ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ይምሕር ፡ ወለዘፈቀደ ፡ ያዐፅብ ፡ ለዘሂ ፡ መሐረ ፡ ይምሕሮ ፡ ወለዘሂ ፡ ተሣሃለ ፡ ይሣሃሎ ።

፴፰ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፴፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ኄር ፡ ዘእንበለ ፡ እከይ ፡ ወየዋህ ፡ ዘእንበለ ፡ በቀል ፡ ወዕጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ መዓት ፡ ጻድቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ወንጹሕ ፡ ዘእንበለ ፡ ርስሐት ፡ ወራትዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ጥውዕየት ።

፵ ፡ ወሀቢ ፡ ዘእንበለ ፡ ክልአት ፡ ወጸጋዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ደንፅዎ ፡ ሠራዬ ፡ ኃጢአት ፡ ዘእንበለ ፡ ቂም ፡ ወቅንዓት ።

፵፩ ፡ ቅሩብ ፡ ውእቱ ፡ ለእለ ፡ ይጼውዕዎ ፡ ወገባሬ ፡ ሠናያት ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ፡ አንቀጽ ፡ ርኅው ፡ ለእለ ፡ ይጐደጕድዎ ፡ ፍኖት መጽያሕት ፡ ዘእንበለ ፡ ማዕቅፍ ፡ ወዐሠር ፡ ንጹሕ ፡ ዘእንበለ ፡ አሥዋክ ።

፵፪ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ አማልክት ፡ ወእግዚአ ፡ አጋዕዝት

፵፫ ፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ ኢባቍዕ ፡ ለአድኅኖተ ፡ ዓለም ፡ ደመ ፡ ነቢያት ፡ ቅዱሳን ፡ እምደመ ፡ አቤል ፡ ጻድቅ ፡ እስከ ፡ ደመ ፡ ዘካርያስ ፡ ወልደ ፡ በራክዩ ፡ ፈነወ ፡ ለነ ፡ ወልዶ ፡ መድኅነ ፡ ወመቤዝወ ፡ ከመ ፡ ይባልሕ ፡ ወይቤዙ ፡ ወያብእ ፡ ቅድሜሁ ፡ ተዝካረ ፡ ሕያዋን ፡ ወሙታን ።

፵፬ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በእንተ ፡ ብፁዕ ።

፵፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡

፵፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ መሐሮሙ ፡ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡

፴፮ ፡ እንዳሰበ ፡ ያደርጋል ፡ እንደ ፡ ጀመረም ፡ የጀመረውን ፡ ይፈጽማል ፡ እንደ ፡ ወደደም ፡ ያከናውናል ። ያሳዝናል ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ ያደኸያል ፡ ባለጸጋም ፡ ያደርጋል ። ያዋርዳል ፡ ያከብራል ፡ ይገድላል ፡ ያድናልም ፡ ድውይ ፡ ያደርጋል ፡ ይፈውሳልም ፡ ይኰንናል ፡ ያጸድቃልም ።

፴፯ ፡ የወደደውን ፡ ይምራል ፡ ሊያስጨንቀው ፡ የወደደውን ፡ ያስጨንቃል ፡ የሚምረውን ፡ ይምረዋል ፡ ይቅር ፡ የሚለውን ፡ ይቅር ፡ ይለዋል ።

፴፰ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ በደላችን፡ አይደለም ።

፴፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ክፋት ፡ የሌለበት ፡ ቸር ፡ በቀል ፡ የሌለበት ፡ የዋህ ፡ ቁጣ ፡ የሌለበት ፡ ትዕግሥተኛ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ ጻድቅ ፡ እድፍ ፡ የሌለበት ፡ ንጹሕ ፡ ጠማምነት ፡ የሌለበት ፡ ቅን ፡ ነው ።

፵ ፡ ያለ ፡ መከልከል ፡ ሰጪ ፡ ያለ ፡ መንፈግ ፡ ለጋስ ፡ ያለ ፡ ቂምና ፡ ያለ ፡ ቅናት ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያስተሠርይ ፡ ነው ።

፵፩ ፡ ለሚጠሩት ፡ ሰዎች ፡ የቀረበ ፡ ነው ፡ ለሚፈሩትም ፡ በጎውን ፡ ነገር ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ፡ ለሚመቱት ፡ ሰዎች ፡ የተከፈተ ፡ ቢር ፡ ነው ። ያለ ፡ መሰናክል ፡ ጥርጊያ ፡ ጐዳና ፡ እሾህ ፡ የሌለበት ፡ ንጹሕ ፡ ፍለጋ ፡ ነው ።

፵፪ ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ የአጋዕዝት፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፵፫ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከአቤል ፡ ደም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ በራክዩ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ዘካርያስ ፡ ደም ፡ ድረስ ፡ የቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ ደም ፡ ዓለምን ፡ ለማዳን ፡ እንዳልጠቀመ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ቤዛ ፡ መድኃኒት ፡ የሚሆን ፡ ልጁን ፡ ሰደደልን ፡ ፈጽሞ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ በፊቱ ፡ የሕያዋንንና ፡ የሙታንን ፡ መታሰቢያም ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ።

፵፬ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በእንተ ፡ ብፁዕ ፡ (ቅዳሴ ፡ ሐዋ ፡ ቍ ፡ ፮—፱ ።)

፵፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ቅዳሴ ፡ ሐዋ ፡ ፲—፳፩ ።)

፵፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ አቤቱ ፡ የጳጳሳቱን ፡ አለቆች ፡ ጳጳሳቱንና ፡ ኤጲስቆጶሳቱን ፡

ኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

፵፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ መጽአ ፡ እንዘ ፡ ሀልው ፡ በህየ ፡ ወተፈነወ ፡ እንዘ ፡ ኢይደምዕ ፡ በዝየ
፵፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ተንሥኡ ።
፵፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ወረደ ፡ እንዘ ፡ ኢይትሐወስ ፡ እመንበሩ ፡ ወኢያንቀለቅል ፡ እመካኑ።
፶ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ውስተ ፡ ጽባሕ ፡ ነጽሩ ።

፶፩ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ተፀንሰ ፡ በከርሥ ፡ እንዘ ፡ ምሉዕ ፡ በኵለሄ ፡ ወተወልደ ፡ እንዘ ፡ ኢያርኁ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልና ።
፶፪ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንነጽር ።
፶፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ተሐፅነ ፡ ከመ ፡ ሕፃን ፡ ወልሕቀ ፡ በበሕቅ ፡ እስከ ፡ ወርዘወ ፡ በአምጣነ ፡ ብእሲ ።
፶፬ ፡ በ፴ ፡ ክረምት ፡ በዮርዳኖስ ፡ ተጠምቀ ፡ ከመ ፡ ያንጽሖን ፡ እምኃጢአት ፡ በሕፅበተ ፡ ዳግም ፡ ልደት ።
፶፭ ፡ እምነበ ፡ ዲያብሎስ ፡ ተመከረ ፡ ርኅበ ፡ ወጸምዐ ፡ አንሶሰወ ፡ ወአስተርአየ ፡ እንዘ ፡ ይሰብክ ፡ ወንጌለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።
፶፮ ፡ በዝየ ፡ ዕርገተ ፡ ዕጣን ።
ይ ፡ ሕ ፡ ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ።

፶፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ወእምዝ ፡ ሰፍሐ ፡ እደዊሁ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ለሕማም ፡ ከመ ፡ ይፈውስ ፡ ቍስለ ፡ ሕሙማን ፡ በንዝኃተ ፡ ደሙ

፶፰ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ ለጸቢሐ ፡ ዐርብ ፡ አመ ፡ ረፈቀ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አልዓዛር ፡ ዐርኩ ።
፶፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ አንሥኡ ፡ እደዊክሙ ፡ ቀሳውስት ።
፷ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ነሥአ ፡ በእደዊሁ ፡ ኅብስተ ፡ ሥርናይ ፡ ናዕተ ፡ እምዘ ፡ አምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ለድራር ።
በዝየ ፡ ያንሥእ ፡ ኅብስተ ።
፷፩ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።
፷፪ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ አእኲቱ ፡ ባረከ።
፲ቱ ፡ ጊዜ ፡ ወፈተተ ።

ቀሳውስቱንና ፡ ዲያቆናቱን ፡ የክርስቲያን ንም ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ማራቸው ፡ ይቅርም ፡ በላቸው ።
፵፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ በወዲያ ፡ ሳለ ፡ መጣ ፡ በወዲህም ፡ ሳይሰማ ፡ ተላከ ።
፵፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ የተቀመጣችሁ ፡ ተነሡ ።
፵፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ከዙፋኑ ፡ ሳይነቃነቅ ፡ ከበታውም ፡ ሳይናወጥ ፡ ወረደ ።
፶ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ተመልከቱ ።
፶፩ ፡ ይ ፡ ካ ፡ በሁሉ ፡ ምሉዕ ፡ ሲሆን ፡ በማኅፀን ፡ ተፀነሰ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልና ፡ ሳይከፍት ፡ ተወለደ ።
፶፪ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እናስተውል ።
፶፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ አደገ ፡ በሰውመጠን ፡ እስኪጐለምስ ፡ ድረስ ፡ በጥቂቱ ፡ አደገ ።
፶፬ ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ፡በዮርዳኖስ፡ተጠመቀ ፡ በሁለተኛ ፡ ልደት ፡ መታጠብ ፡ ከኃጢአት ፡ ያነጻን ፡ ዘንድ ።
፶፭ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ዘንድ ፡ ተፈተነ ፣ ተራበ ፡ ተጠማም ፡ የሰማይ ፡ መንግሥት ፡ ወንጌልን ፡ እያስተማረ ፡ ታይቶ ፡ ተመላለሰ

፶፮ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቄሱ ፡ ዕጣኑን ፡ ያሳርግ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ በመንግሥትህ ፡ አስበን
(ቅዳሴ ፡ ሐዋ ፡ ፴፩ ።)
፶፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሕማም ፡ በዕፀ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ለጆን ፡ ዘረጋ ፡ በደሙ ፡ መረጨት ፡ የሕሙማንን ፡ ቍስል ፡ ያድን ፡ ዘንድ ።
፶፰ ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ለዐርብ ፡ አጥቢያ ፡ ኀሙስ ፡ ማታ ፡ በወዳጁ ፡ በአልዓዛር ፡ ቤት ፡ በተቀመጠ፡ ጊዜ ።
፶፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ቀሳውስት ፡ እጆቻችሁን ፡ አንሡ ።
፷ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ ለራት ፡ ካመጡለት ፡ ያልመጠጠውን ፡ የስንዴውን ፡ ኅብስት ፡ በእጁ ፡ ያዘ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኅብስቱን ፡ ያንሣ ።

፷፩ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ እናምናለን ፡ ይህ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕውነት ፡ እናምናለን ።
፷፪ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አመሰገነ ፡ ባረከ ። ሦስት፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፡ ፈረሰም ።

ወእምዝ ፡ ያንቅዖ ፡ ለኅብስት ፡ ኅበ ፡ ፭ ፡ ገጽ ፡ ንስቲት ፡ እንዘ ፡ ኢይሌልዮ ።

**ወወሀቦሙ ፡ ለእሊአሁ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡ ብልዑ ፡ ዝ ፡ ኅብስት ፡** «እማሬ፡» **ሱታፌ ፡ ሥጋየ ፡ ውእቱ ፡ ዘይትፌተት ፡ በእንቲአክሙ ።**

፺፫ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ **አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ ንሴብሓከ ፡ አ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።**

፺፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ **ወካዕበ ፡ ቶስሐ ፡ ጽዋዐ ፡ ወይነ ፡ ምስለ ፡ ማይ ፡ አእኰተ ፡ ባረከ ። ቡራኬ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ፡ ወቀደሰ ፡ ወመጠዎሙ ለሐዋርያቲሁ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡ ስትዩ ፡ ዝ ፡ ጽዋዕ ፡** «እማሬ፡» **ሱታፌ ፡ ደምየ ፡ ውእቱ ፡ ዘይትከዐው ፡ በእንቲአ**

ወይነክንከ ፡ ለጽዋዕ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ በእዴሁ ፡ ዘየማን ።

፺፭ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ **አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡**

፺፮ ፡ ይ ፡ ካ ፡ **ወዝንቱ ፡ ሥርዓት ፡ ይኩንክሙ ፡ ለተዝካረ ፡ ሞትየ ፡ ወትንሣኤየ ፡**

፺፯ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ **ንዜኑ ፡ ሞተከ ፡ እግዚኦ ፡ ወትንሣኤከ ፡ ቅድስተ ፡ ነአምን ፡ ዕርገተከ ፡ ወዳግመ ፡ ምጽአተከ ፡ ንሴብሓከ ፡ ወንትአመነከ ፡ ንስእለከ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡ አ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ።**

፺፰ ፡ ይ ፡ ካ ፡ **ወንሆነ ። እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ንስእለከ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡ ወነኀሥሥ ፡ እምነ ፡ ኂሩትከ ፡ አ ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትፈኑ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ወኃይለ ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ ኅብስት ፡** «እማሬ፡» **ወላዕለ ፡ ዝ ፡ ጽዋዕ ፡** «እማሬ፡»

ይረስዮ ፡ ለዝንቱ ፡ ኅብስት ። (ቡራኬ ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ) ። ሥጋ ፡ ዚአከ ፡ ቅዱስ ፡ ወለዝ ፡ ጽዋዕ ። (ቡራኬ ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ።) **ደመ ፡ ገቦከ ፡ ነባቤ ።** (ወዓዲ ፡ ላዕለ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ።)

ይ ፡ ሕ ፡ **አሜን ፡ እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ እግዚኦ ፡ መሐከነ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሃለነ ።**

፺፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ **በኵሉ ፡ ልብ ፡ ናስተብቍዖ**

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኅብስቱን ፡ ሳይለየው ፡ ከአምስት ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ያንቃው ።

**ይህ ፡ ኅብስት ፡** «እማሬ፡» **ስለናንተ ፡ ከሚፈተት ፡ ሥጋዬ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ንሡ ፡ ብሎ ፡ ለወገኖቹ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሰጣቸው ።**

፺፫ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ **አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ እናምናለን ፡ እንታመናለንም ፡ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እናመሰግንሃለን ፡ ይህ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕውነት ፡ እናምናለን ።**

፺፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ **ዳግመኛም ፡ የወይን ፡ ጽዋ ፡ ከውኃው ፡ ጋራ ፡ ቀላቅሎ ፡ አመሰገነ ፡ ባረከ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፡ አከበረ ፡ ይህ ፡ ጽዋ ፡** «እማሬ፡» **ስለናንተ ፡ ከሚፈስ ፡ ደሜ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ንሡ ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሰጣቸው ።**

በቀኝ ፡ እጁ ፡ ጽዋውን ፡ በዐራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ይወዝውዘው ።

፺፭ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ **አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ።**

፺፮ ፡ ይ ፡ ካ ፡ **ይህም ፡ ሥርዓት ፡ ለሞቴና ፡ ለትንሣኤዬ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሁናችሁ ።**

፺፯ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ **አቤቱ ፡ ሞትህን ፡ ቅድስት ትንሣኤህንም ፡ እንናገራለን ። ዕርገትህን ፡ ዳግመኛም ፡ መምጣትህን ፡ እናምናለን ፡ እናመሰግንሃለን ፡ እናምንሃለንም ፡ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንለምንሃለን ፡ እንማልድሃለንም ።**

፺፰ ፡ ይ ፡ ካ ፡ **እኛም ፡ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ እንለምንሃለን ፡ እንማልድሃለንም ። ሰውን ፡ የምትወድ ፡ ሆይ ፡ ከቸርነትህ ፡ እንሻለን ፡ ወደዚህ ፡ ኅብስት** «እማሬ፡» **ወደ ፡ ዚህም ፡ ጽዋ ፡** «እማሬ፡» **መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ኃይልንም ፡ ትሰድ ፡ ዘንድ ።**

ይህን ፡ ኅብስት ። (አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ።) ያንተን ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋ ፡ ይህንም ፡ ጽዋ ።

**አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፡ ነባቢ ፡ የሚሆን ፡ የጐንህን ፡ ደም ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ። ዳግመኛም ፡ ሁለቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ።**

ይ ፡ ሕ ፡ **አቤቱ ፡ ማረን ፡ አቤቱ ፡ ራራልን አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።**

፺፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ **በፍጹም ፡ ልብ ፡ አምላካችንን ፡**

ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ኅብረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠናየ ፡ ከመ ፡ ይጸግወነ ።

፴፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ሀሎ ፡ ሀልወ ፡ ወይሄሉ፡ለትውልደ፡ትውልድ፡ ለዓለመ፡ ዓለም ።

፴፬ ፤ በዝየ ፡ ይኀትም ፡ ሥጋ ፡ በደም ፡ ጠሚሮ ፡ በአጽባዕቱ ።

ይ ፡ ካ ፡ ደሚረከ ፡ ተሀብ ፡ ለእለ ፡ ይነሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ ይኩኖሙ ፡ ለበረከት ፡ ወለሥርየተ ፡ ኃጢአት ፡ ለፍሥሓ ፡ ወለኀሤት ፡ ለሐድሶ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ወመንፈስ ፡ ወአጽንዖ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ እስትንፋስ ፡ ደኃሪት ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

፴፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ሀበነ ፡ ንኅበር ፡ በዘዚአከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ወፈውሰነ ፡ በዝንቱ ፡ ጵርስፎራ ፡ ከመ ፡ ብከ ፡ ንሕየው ፡ ዘለኵሉ ፡ ዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፴፮ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ቡሩክ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይትባረክ ፡ ስመ ፡ ስብሓቲሁ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ፡ ቡሩክ ፡ ለይኩን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፴፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ፈኑ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ላዕሌነ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፴፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሃለነ ።

ይ ፡ ካ ፡ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፴፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ፈትቶ ።

አይቴ ፡ ብሔራ ፡ ለጥበብ ፡ ወአይቴ ፡ ማኅደራ ፡ አይቴ ፡ ደወላ ፡ ወበአይቴ ፡ ተረክበ ፡ ዐሠረ ፡ ፍኖታ ።

፵ ፤ መኑ ፡ ዐደወ ፡ ባሕረ ፡ ወተሣየጣ ፡ በወርቅ ፡ ቀይሕ ፡ ወመኑ ፡ ዐርገ ፡ መልዕልተ ፡ ደመናት ፡ ወአውረዳ ፤ ኢየአምራ ፡ መዋቲ ፡ ለፍኖታ ፡ ወኢሀለወት ፡ ነበ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፵፩ ፤ ተረስአት ፡ እምኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወተኀብአት ፡ እምኵሉ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ። እለ ፡

እግዚአብሔርን ፡ እንለምነው ። ያማረ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አንድነት ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ።

፴፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ በፊት ፡ እንደነበረ ፡ ለዘላለሙ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ።

፴፬ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡ ጠምቶ ፡ በደሙ ፡ ሥጋውን ፡ ይቀባ ።

ይ ፡ ካ ፡ ከእርሱ ፡ ለሚቀበሉት ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ስጥ ። ለበረከትና ፡ ለኃጢአት የማስተሥረያ ፡ ለፍጹም ፡ ደስታም ፤ ነፍስንና ፡ ሥጋን ፡ መንፈስንም ፡ ለማደስ ፤ እስከ ኋላኛዪቱ ፡ እስትንፋስ ፡ ድረስ ፡ ሃይማኖትን ፡ ለማጽናት ፡ ይሆናቸው ፡ ዘንድ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

፴፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ የአንተ ፡ በሚሆን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ መሆንን ፡ ስጠን ፡ በዚህም ፡ ጵርስፎራ ፡ (ኅብስት ፡) አድነን ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በምትሆን ፡ በአንተ ፡ ለዘላለሙ ፡ ሕያዋን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

፴፮ ፤ ይ ፡ ካ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስሙ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚመጣውም ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ የጌትነቱ ፡ ስም ፡ ይመስገን ፤ ይሁን ፡ ይሁን ፡ የተመሰገነ ፡ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፤ እንደርሱ ።

፴፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ የመንፈስህን ፡ ጸጋ ፡ ላክልን

፴፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፡ ሰላም ፡ ለሁላችሁ ፡ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።

፴፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ የመፈተት ፡ ጸሎት ።

የጥበብ ፡ አገሯ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ማደሪያዋስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ቦታዋ ፡ ወዴት ነው ፡ የጐዳናዋስ ፡ ፍለጋ ፡ በወዴት ፡ ተገኘ

፵ ፤ ባሕሩን ፡ ተሻግሮ ፡ በቀይ ፡ ወርቅ ፡ የገዛት ፡ ማነው ፤ ከደመናትስ ፡ በላይ ፡ ወጥቶ ፡ ያወረዳት ፡ ማነው ፤ መዋቲ ፡ ጐዳናዋን ፡ አያውቃትም ። በሰውም ፡ ዘንድ ፡ የለችም ።

፵፩ ፤ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ተዘነጋች ፤ ከሰማይ፡ አዕዋፍም ፡ ሁሉ ፡ ተሠወረች ፤ እርሷን ፡

ኪያሃ ፡ አጥረዩ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተዐረኩ ። ወእለ ፡ ይጸልዕዋ ፡ ያፈቅሩ ፡ ሞተ ፡ ትልሒ ፡ እምፀሓይ ፡ ወእምኵሉ ፡ ንብረተ ፡ ከዋክብት ። ወምስለ ፡ ብርሃን ፡ እንዘ ፡ ትትቃወም ፡ ትትረከብ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚት ፡ይእቲ

፹፱ ፡ ወእንዘ ፡ በርሥእ ፡ ሀለወት ፡ ኵሎ ፡ ትሔድስ ፡ ወበበትውልድ ፡ ውስተ ፡ ነፍሰ ፡ ጻድቃን ፡ ትትፋለስ ።

፺ ፡ ይእቲ ፡ ትኄይስ ፡ እምዕንቍ ፡ ክቡር ወኵሉ ፡ ክብር ፡ ኢመጠና ፡ ላቲ ፡ ምክር ፡ ወእዘዝ ። ወላቲ ፡ ጽንዕ ፡ ወአእምሮ ፡ ወባቲ ፡ ነገሥት ፡ ይነግሡ ፡ ወባቲ ፡ ኃያላን ፡ ይጽሕፉ ፡ ጽድቀ ።

፺፩ ፡ ባቲ ፡ ዐቢያን ፡ ይከብሩ ፡ ወባቲ ፡ መኳንንት ፡ ይእኅዙ ፡ ምድረ ። እለ ፡ ያፈቅርዋ ፡ ታፈቅር ፡ ወእለ ፡ የዐቅብዋ ፡ ተዐቅብ ፡ ወእለ ፡ ኪያሃ ፡ የኅሥሡ ፡ ይረክቡ ፡ ሞገሰ ።

፺፪ ፡ ውስተ ፡ ፍናወ ፡ ጽድቅ ፡ ታንሶሱ ፡ ወውስተ ፡ ዐሠረ ፡ ጽድቅ ፡ ትትመያየጥ ፡ ከመ ፡ ተሀቦሙ ፡ ለእለ ፡ የአምርዋ ፡ ጥሪተ ፡ ወመዛግብቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ትምላዕ ፡ ተድላ ።

፺፫ ፡ ዘኵሎ ፡ የአምር ፡ ውእቱ ፡ አእመራ ፡ ወዘኵሎ ፡ ይጤይቅ ፡ ውእቱ ፡ አሠነየ ፡ ፍኖታ ፡ ውእቱ ፡ ወሀቦ ፡ ለያዕቆብ ፡ ቍልዔሁ ፡ ወለእስራኤል ፡ ቅዱሱ ፡ ወእምዝ ፡ አስተርአየት ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወአንሶሰወት ፡ ከመ ፡ ዕጓለ ፡ ሕመሕያው ።

፺፬ ፡ ናሁ ፡ ሐነጸት ፡ ላቲ ፡ ቤተ ፡ ወዐቀመት ፡ ፯ተ ፡ አዕማደ ፡ ዘብሐት ፡ ዘዚአሃ ፡ ጥብሐ ፡ ወቶስሐት ፡ ውስተ ፡ ስያሐ ፡ ዘዚአሃ ፡ ወይነ ፡ ወአስተዳለወት ፡ ዘዚአሃ ፡ ማዕደ ።

፺፭ ፡ ፈነወት ፡ ዘዚአሃ ፡ አግብርተ ፡ በነዋኅ ፡ ሰብከት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ዘአብድ ፡ ውእቱ ፡ ይትገሐሥ ፡ ኀቤየ ። ወለእለሂ ፡ የሐጽጾሙ ፡ አእምሮ ፡ ትጼውዕ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ንዑ ፡ ብልዑ ፡ ኅብስትየ ፡ ወስትዩ ፡ ወይንየ ፡ ወኅድግዋ ፡ ለእበድ ፡ ወሕየዉ ።

እርስዋን ፡ የገዙ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ተወዳጁ ። እርሷን ፡ የሚጠሏት ፡ ሞትን ፡ ይወዳሉና ፡ከፀሐይ ፡ ይልቅ ፡ ታምራለች ፡ ከከዋክብትም ፡ አኗኗር ። እርሷ ፡ ቀዳማዊት ፡ እንደ ፡ መሆንዋ ፡ ከብርሃን ፡ ጋራ ፡ ስትነጻጸር ፡ ትገኛለች ።

፹፱ ፡ በእርጅና ፡ ሳለች ፡ ሁሉን ፡ ታድሳለች ፡ በየትውልዱም ፡ በጻድቃን ፡ ሰውነት ፡ ትፋለሳለች ።

፺ ፡ ከከበረ ፡ ዕንቍ ፡ እርሷ ፡ ትበልጣለች ፡ ክብርም ፡ ሁሉ ፡ መጠንዋ ፡ አይደለም ፡ ምክር ፡ ዕውቀት ፡ አላት ፡ ጽንዕ ፡ አእምሮም ፡ አላት ፡ ነገሥታቱም ፡ በእርሷ ፡ ይነግሣሉ ፡ ኃያላንም ፡ በእርሷ ፡ ዕውነትን ፡ ይጽፋሉ ።

፺፩ ፡ ደጋጎች ፡ በእርሷ ፡ ይከበራሉ ፡ መኳንንትም ፡ በእርሷ ፡ ምድርን ፡ ይይዛሉ ፡ የሚወዷትን ፡ ትወዳለች ፡ ሕጓን፡ የሚጠብቁትንም ፡ ትጠብቃለች ፡ እርሷንም ፡ የሚሹ ፡ ባለሟልነትን ፡ ያገኛሉ ።

፺፪ ፡ በዕውነት መንገዶች ፡ ትመላለሳለች ፡ በዕውነት ፍለጋም ፡ ትመላለሳለች ፡ ለሚያውቋት ፡ ሰዎች ፡ ብዕልን ፡ ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ መዝገባቸውንም ፡ ተድላን ፡ ትመላ ፡ ዘንድ ።

፺፫ ፡ ሁሉን ፡ የሚያውቅ ፡ እርሱ ፡ ያውቃታል ። ሁሉን ፡ የሚረዳ ፡ እርሱ ፡ ጎዳናዋን ፡ አሳመረ ፡ እርሱ ፡ ለባለሟሉ ፡ ለያዕቆብ ፡ ለቅዱሱም ፡ ለእስራኤል ፡ ሰጠው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ታየች ፡ እንደ ሰውም ፡ ተመላለሰች ።

፺፬ ፡ እነሆ ፡ ቤትን ፡ ሠራች ፡ ሰባት ፡ አዕማድንም ፡ አቆመች ፡ የርሷን ፡ እርድ ፡ አረደች ፡ በማድጋዋም ፡ የርሷን ፡ ወይን ፡ ጨመረች ፡ የርስዋንም ፡ ማዕድ ፡ አዘጋጀች ።

፺፭ ፡ ባሮቿን ፡ ላከች ፡ በረጅም ፡ ስብከት ፡ ሰነፍ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወደኔ ፡ ይምጣ ፡ እያለች ፡ ዕውቀት ፡ ያነሳቸውንም ፡ ትጠራለች ፡ ኑ ፡ የኔን ፡ ኅብስት ፡ ብሉ ፡ የኔን ፡ ወይንም ፡ ጠጡ ፡ ስንፍናንም ፡ ትታችሁ ፡ ኑሩ ፡ እያለች ።

፹፮ ፤ ጥበብሰ ፡ መድኃኒነ ፡ ውእቱ ፡ ዘቤዘወነ ፡ በጥብሐ ፡ ሥጋሁ ፡ ወተሣየጠነ ፡ በንዝኅተ ፡ ደሙ ፡ ወኀረየነ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፹፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቡነ፡ ዘበሰማያት ።

፹፰ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘብርሃናት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሥልጣናት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአርእስተ ፡ መላእክት ። ነፍስ ፡ እንተ ፡ ተአሥረት ፡ በሞት ፡ ፈታሕከ ፡ ወዘተቀነወ ፡ በጽልመት ፡ በቅንዋተ ፡ መስቀሉ ፡ ለዋሕድከ ፡ አብራህከ ።

፹፱ ፤ ዘፈትሐ ፡ ሕማማተ ፡ ዚአነ ፡ወኵሎ ክበደነ ፡ አሰሰለ ፤ ወኵሎ ፡ ማእሠረ ፡ ኃጢአትነ ፡ ፈትሐ ። ዘቅጥቃጤ ፡ ዚአነ ፡ ነሣእከ ፡ እግዚኦ ፡ ወአሕየውከነ ፡ ወኮንከ ፡ ለነ ፡ ፍኖተ ፡ መካነ ፡ ሕይወት ፡ እሙስና ፡ ውስተ ዘኢይማስን ፡ ሜጥከነ ።

፺ ፤ እግዚኦ ፡ አምላክነ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመንጦላዕቱ ፡ ብርሃን ፡ ወቅድመ ፡ ገጹ ፡ እሳት ፡ ወመንበረ ፡ ስብሓቲሁ ፡ ዘኢይትረክም ፡ ወምዕራፈ ፡ ተድላሁ ፡ ዘኢይትነገር ፡ ዘአስተዳለወ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወመልበስቱ ፡ መዛግብተ ፡ ብርሃን ፡

፺፩ ፤ ወቅዱሳነ ፡ መላእክተ ፡ ትርዒ ፡ ዘይርዕድ ፡ ወይዌድስ ፡ ኵሉ ፡ በነጽሮ ፡ ይመስዎሙ ፡ ለአድባር ፡ ወስሙሂ ፡ ተነጊሮ ፡ ይነቅዕ ፡ ማዕምቅት ።

፺፪ ፤ ዘሰማያተ ፡ ከደንከ ፡ አስተጋቢኦከ ፡ በእድ ፡ ዘምድር ፡ ትርዕድ ፡ ወቀላይት ፡ ኀቡረ ።

፺፫ ፤ ዘቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊተ ፡ ጸላዒ ፡ ይትመነደቡ ፡ ዲያብሎስ ፡ ወድቀ ፡ ወአርዌ ፡ ተከይደ ፡ ወከይሲ ፡ ተኀጕለ ።

፺፬ ፤ ወዘቦቱ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ብከ ፡ በርሁ ፡ ወጸንዑ ፡ ብከ ፡ እግዚኦ ፡ ዘብከ ፡ ተርእየ ፡ ሕይወት ፡ ወተስፋ ፡ ጸንዐ ፤ ወወንጌል ፡ ተሰብከ ፡ ዘቦቱ ፡ ማሰነ ፡ ሙስና ወዘኢይማስን ፡ ጸንዐ ።

፹፮ ፤ ጥበብ ፡ ግን ፡ መድኃኒታችን ፡ ነው በሥጋው ፤ መሥዋዕትነት ፡ ያዳነን ፤ በደሙም ፡ ፈሳሽነት ፡ የተወጀጀን ፡ ለመንግሥቱም ፡ የመረጠን ፤ ለዘላለሙ ።

፹፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ።

፹፰ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የብርሃናት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሥልጣናት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሊቃነ ፡ መላእክት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሞት ፡ ታሥራ ፡ የነበረች ፡ ነፍስን ፡ ፈታህ ። በጨለማ ፡ የተቸነከረውንም ፡ በአንድ ፡ ልጅህ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ መቸንከር ፡ አበራህ ።

፹፱ ፤ የኛን ፡ ሕማማት ፡ የፈታ ፡ ሸክማችንንም ፡ ሁሉ ፡ ያራቀ ፤ የኃጢአታችንን ፡ ማሠሪያነት ፡ ሁሉ ፡ የፈታ ፤ አቤቱ ፡ የእኛን ፡ መከራ ፡ መቀጥቀጥ ፡ ወስደህ ፡ ያዳንኸን ፡ የሕይወት ፡ ቦታ ፡ ጎዳና ፡ የሆንህልን ፡ ከጥፋት ፡ ወደማይጠፋ ፡ ጽድቅ ፡ የመለስከን ።

፺ ፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሁሉን ፡ የያዝህ ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ መጋረጃው ፡ ብርሃን ፤ ፊቱ ፡ እሳት ፡ የጌትነቱም ፡ ዙፋን ፡ የማይመረመር ፤ ለቅዱሳን ፡ ያዘጋጀው ፡ የተድላው ፡ ማረፊያም ፡ የማይነገር ፤ ልብሱ ፡ የብርሃን ፡ መዝገብ ፡ የሚሆን ።

፺፩ ፤ ቅዱሳን ፡ መላእክትንም ፡ ትጠብቃለህ ፡ ሁሉ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ በማየት ፡ የሚያመሰግንህ ፡ ተራራዎቹን ፡ ያቀልጣቸዋል ፤ ስሙም ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ጥንጯው ፡ ይሠነጠቃል ።

፺፪ ፡ ሰማያትን ፡ በእጅ ፡ ሰብስበህ ፡ ያለበስህ ። ምድር ፡ የምትንቀጠቀጥልህ ፡ ቀላያትም ፡ በአንድነት ።

፺፫ ፡ በእርሱ ፡ የጠላት ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ የተቸገሩ ፤ ዲያብሎስ ፡ ወደቀ ፡ አርዌ ፡ ተረገጠ ፤ ከይሲም ፡ ጠፋ ።

፺፬ ፤ በአንተ ፡ ያመኑ ፡ አሕዛብ ፡ በርሱ ፡ ብርሃን ፡ የሆኑ ፤ አቤቱ ፡ በአንተም ፡ የጸኑ ፡ ሕይወት ፡ በአንተ ፡ የተገለጸ ፤ ተስፋም ፡ የጸና ፤ ወንጌልም ፡ የተሰበከ ፤ በርሱ ፡ ጥፋት የጠፋ ፡ የማይጠፋውም ፡ የጸና ።

፺፭ ፤ እግዚኦ ፡ አምላክነ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡
ረስየነ ፡ ድልዋነ ፡ ንንሣእ ፡ እምዝንቱ ፡ ኅብ
ስት ፡ «እማሬ ፡» ሥጋ ፡ ወልድከ ፡ ማኅየዊ ፡
ወእምዝንቱ ፡ ጽዋዕ ፡ «እማሬ ፡» ደመ ፡
መሢሕከ ፡ ነባቢ ፡ ዘቦቱ ፡ ለከ ፡ ምስሌሁ ፡
ወምስለ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ስብሐት ፡ ወእ
ኂዝ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡
ዓለም ፡ አሜን ።

፺፮ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክቲሁ ፡
ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፤ ይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ፡
ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።
ወይኬልልዎ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፤
ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።
ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለመድኃኔ ፡ዓለም
በአማኑ ፡ ዚአሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንገኒ ።
፺፯ ፤ ይ፡ ዲ፡ ንፍቅ አርኅዉ ፡ ኆኃተ ፡ መኳን
ንት ።
፺፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ትቀውሙ ፡ አትሕቱ ፡
ርእሰክሙ ።
፺፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በግዕ ፡ ይምጻእ ፡ ንርአዮ ፡
በአዕይንት ፡ ወንጥብሖ ፡ በአእዳው ፡ ከመ ፡
ንትፈሣሕ ፡ ቦቱ ፡ ይደመር ፡ ሥጋሁ ፡
ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ኅብስት ። ወደሙኒ ፡ ይት
ከዐው ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ጽዋዕ ።

፻ ፤ ወኢይምስሎ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔነ ፡ ሶበ ፡
ይበልዕ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ «እማሬ ፡» ከመ ፡
ዘይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ደም ፡
ወመንፈስ ፤ ወሶበ ፡ ይሰቲ ፡ ዘንተ ፡ ጽዋዐ ፡
«እማሬ ፡» ኢይምስሎ ፡ ለ፩ዱ፡እምኔነ ፡ከመ፡
ዘይሰቲ ፡ ደመ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋ ፡
ወመንፈስ፤ አላ ፡ ፩ዱ፡ውእቱ ፡ ሥጋ፡ ወደም
ወመንፈስ ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ መለኮቱ ፡ ዘም
ስለ ፡ ትስብእቱ ፡ ፩ደ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
፻፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
በፍርሃት ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡
ወንሴብሐከ ።
፻፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሐ ።
፻፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ነጽር ።
ይ ፡ ካ ፡ ቅድሳት ፡ ለቅዱሳን ።
ይ ፡ ሕ ፡ ፩ዱ፡አብ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ፡ ወልድ፡
ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፺፭ ፡ ሁሉን ፡ የያዝህ ፡ አምላካችን ፡
አቤቱ ፡ ማኅየዊ ፡ ከሚሆን ፡ ከልጅህ ፡ ሥጋ
ከዚህ ፡ ኅብስትና ፡ «እማሬ ፡» የመሢሕህ ፡
ነባቢ ፡ ደም ፡ ከሆነ ፡ ከዚህም ፡ ጽዋ ፡
«እማሬ ፡» እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ የተዘጋጀን ፡
አድርገን ። በርሱ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ጽንዕ ፡
ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡
ለአንተ ፡ ይገባል ፤ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘ
ላለሙ ፡ አሜን ።
፺፮ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ የመላ
እክት ፡ ሠራዊት ፡ በመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡
ይቆማሉ ።
መድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ያመሰግኑታል ፤ የመ
ድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ሥጋውና ፡ ደሙ ።
ከመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡ እንድረስ ፤
እርሱን ፡ በማመን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንገዛለን ።
፺፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ መኳንንት ፡ ደጆ
ችን ፡ ክፈቱ ።
፺፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ የቆማችሁ ፡ ሰዎች ፡ ራሳች
ሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ።
፺፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ በግዕ ፡ ይምጣ ፤ በዓይናችን ፡
እንድናየው ፤ በእጃችንም ፡ እንድናርደው ፡
በእርሱ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ ሥጋው ፡
ከዚህ ፡ ኅብስት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይሁን ፡
ደሙም ፡ በዚህ ፡ ጽዋ ፡ ይቀዳ ።

፻ ፤ ከእኛ ፡ ወገን ፡ ላንዱ ፡ ይህን ፡ ኅብ
ስት ፡ «እማሬ ፡» በሚበላበት ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡
ደምና ፡ ያለ፡መንፈስ፡ሥጋን፡ብቻ ፡ የሚበላ ፤
ይህንም ፡ ጽዋ ፡ «እማሬ ፡» በሚጠጣበት ፡
ጊዜ ፡ ከእኛ ፡ ወገን ፡ ላንዱ ፡ ያለ ፡ ሥጋና ፡
ያለ ፡ መንፈስ ፡ ደምን ፡ ብቻ ፡ የሚጠጣ ፡
አይምሰለው ። ሥጋና ፡ ደም ፡ መንፈስም ፡
አንድ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ። መለኮቱ ፡ ከትስ
ብእቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ለዘላለሙ ።
፻፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ በፍርሃት ፡ ሁናችሁ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ስገዱ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ በፊትህ ፡ እንሰግዳለን ፡
እናመሰግንሃለንም ።
፻፪ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሐ ።
፻፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ተመልከት ።
ይ ፡ ካ ፡ ቅድሳት ፡ ለቅዱሳን ፡ ነው ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነው ፤
ቅዱስ ፡ ወልድ ፡ አንድ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡
ቅዱስም ፡ አንድ ፡ ነው ።

፻፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ፡ኵል ክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፻፭ ፡ ወእምዝ ፡ ያንሥእ ፡ ካህን ፡ ኅብስተ ፡ ፍጹመ ፡ በእደዊሁ ፡ ወይበል ፡ እግዚኦ ፡ መሐ ረነ ፡ ክርስቶስ ፡ ፲ቱ ፡ ጊዜ ፡ በዐቢይ ፡ ዜማ ። ፲ተወሬት ፡ ጊዜ ፡ በንዑስ ፡ ዜማ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

ወእምዝ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ፲ቱ ፡ ጊዜ ። ይ ፡ ሕ ፡ ፪ኤተ ፡ ጊዜ ።

፻፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ንስሓ ፡ ሀለው ክሙ ፡ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ።

ወእምዝ ፡ ተመይጦ ፡ መንገለ ፡ ሕዝብ ።

፻፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ነጽር ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ንስሓ ፡ ሀለዉ ።

ወእምድኅረ ፡ ተመጠዉ ።

፻፰ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ኅዳጌ ፡ ነፍስ ። ወካዕበ፡ ናስተበቍዕ ፡ ዘኵሎ ፡ ይእኀዝ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አብ ፡ ለእግዚእ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ። እስመ ፡ ኢመነነ ፡ ወኢተ ቄጥዐ ፡ ስእለተነ ፡ ወኢየርኀቀ ፡ ግህሎ ፡ እምኔነ ፡ እስመ ፡ መሐሪ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አምላክነ ።

ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

፻፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እወ፡እግዚኦ፡አምላክ፡ኵሉ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ ንጉሠ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ መላኬ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ መድኃኔ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ መኰንነ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ ማኅየዊ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ መጋቤ ፡ ኵሉ ።
እወ ፡ እግዚኦ ፡ መሲስየ ፡ ኵሉ ።

፻፲ ፡ በከመ ፡ ደመርከ ፡ ሥጋ ፡ ወልድከ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ፡ ዚአነ ፡ ወበከመ ፡ ቶሳሕከ፡ ደመ ፡ መሢሕከ ፡ ውስተ ፡ ደመ ፡ ዚአነ፡ ከማሁ ፡ ደምር ፡ ፈሪሆተከ ፡ ውስተ ፡ አልባ ቢነ ፡ ወሥነ ፡ አምልኮትከ ፡ ውስተ ፡ ኅሊ ናነ ።

፻፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።

፻፭ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቄሱ ፡ መላውን ፡ ኅብስት ፡ አንሥቶ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ በከፍ ተኛ ፡ ዜማ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በንዑስ፡ ዜማ ፡ ፲፪ ፡ ጊዜ ፡ አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ፡ ይበል ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ። ይ ፡ ሕ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ።

፻፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በንስሓ ፡ ውስጥ ፡ ያላችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ተመልሶ ።

፻፯ ፡ ይ፡ ካ ፡ አምላካችን፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ በንስሓ ፡ ውስጥ ፡ ወዳሉት ፡ ወገኖ ችህ ፡ ተመልከት ። (ቅዳሴ ፡ ሐዋርያት ፡ ቍ ፡ ፺፫—፻፴፰ ።

ከተቀበሉም ፡ በኋላ ።

፻፰ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ኅዳጌ ፡ ነፍስ ፡ ዳግመኛም ፡ ሁሉን ፡ የሚይዝ ፡ የጌታችን ፡ የመድኃኒታ ችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አባት ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ እንማልዳለን ። ልመናችንን ፡ አልናቀም ፤ አልተቆጣምና ። ይቅርታው ንም ፡ ከኛ ፡ አላራቀምና ፡ አምላካችን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

፻፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አዎን ፡ አቤቱ ፡ የሁሉ ፡ አምላክ ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ የሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ ሁሉን ፡ የያዝህ ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ ሁሉን ፡ የምትገዛ ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ ሁሉን ፡ የምታድን ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ በውነት ፡ የሁሉ ፡ ገዢ ፡ ነህ
አዎን ፡ አቤቱ ፡ የሁሉ ፡ መድኃኒት ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ ሁሉን ፡ የምትጠብቅ ፡ ነህ ።
አዎን ፡ አቤቱ ፡ ሁሉን ፡ የምትመግብ ፡ ነህ ።

፻፲ ፡ የልጅህን ፡ ሥጋ ፡ ከእኛ ፡ ሥጋ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንዳደረግህ ፡ የመሢሕህ ንም ፡ ደም ፡ ከእኛ ፡ ደም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንዳደረግህ ፡ እንዲሁ ፡ አንተን ፡ መፍራ ትን ፡ በልቡናችን ፤ በጎ ፡ አምልኮትህንም ፡ በኅሊናችን ፡ ጨምር ።

፻፲፩ ፤ ንህነሰ ፡ ሥጋውያን ፡ ንኄሊ ፡ ሕገ ፡ ሥጋ ፡ ወንገብር ፡ ግብረ ፡ ሥጋ ፡ ወነሐውር ፡ በፍኖተ ፡ ሥጋ ። አንተ ፡ ባሕቱ ፡ መሀረነ ፡ ምግባረ ፡ መንፈስ ፡ ወአለብወነ ፡ ሕገ ፡ መንፈስ ፡ ወምርሐነ ፡ ለነ ፡ አንተ ፡ ፍኖተ ፡ መንፈስ ።

፻፲፪ ፤ እስመ ፡ ለነ ፡ ለኃጥአን ፡ ለእመ ፡ መሐርከነ ፡ ውእቱ ፡ አሚረ ፡ ትሰመይ ፡ መሐሬ ፤ ወለጻድቃንሰ ፡ እምግባሮሙ ፡ ትምሕሮሙ ፡ ወትዔሥዮሙ ፡ በከመ ፡ ጽድቆሙ

፻፲፫ ፤ ኢትዝክር ፡ ለነ ፡ አበሳነ ፡ ዘትካት ፡ ፍጡነ ፡ ይርከበነ ፡ ሣህልከ ፡ እግዚኦ ።

፻፲፬ ፤ ኀቤከ ፡ ንጸርሕ ፡ ኀቤከ ፡ ነዐውዩ ፡ ኀቤከ ፡ ንትመሀለል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

፻፲፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አንብሮ ፡ እድ ።

ልዑል ፡ ውእቱ ፡ እመልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ኀሊና ፡ ወልቡና ፡ ፈክሮ ፡ ብዕለ ፡ ሀብትከ ፡ አ ፡ ሊቅነ ፡ እስመ ፡ ኀባዕከ ፡ እሎንተ ፡ እምጠቢባን ፡ ወለባውያን ፡ ወከሠትከ ፡ ለሕፃናት ፡ ንዑሳን ።

፻፲፮ ፤ ዘፈተዉ ፡ ነቢያት ፡ ወነገሥት ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ወኢርእዩ ፡ ኪያሆሙ ፡ ጸጎከ ፡ ለነ ፡ ለኃጥአን ፡ ከመ ፡ ንትቀነይ ፡ ወንትቀደስ ፡ ቦሙ ፡ ሶበ ፡ ገበርከ ፡ ለነ ፡ በሥርዓተ ፡ ዋሕድ ፡ ወልድከ ፤ ምሥጢረ ፡ ኅቡእ ፡ ዘኢየዐግቶ ፡ ደመ ፡ ሕግ ፡ ብሉይ ፡ ወኢጽድቅ ፡ ዘሥጋ ፡ አላ ፡ በግዕ ፡ ሰማያዊ ፡ ወመሥዋዕት ፡ ነባቢ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋ ።

፻፲፯ ፤ ዘንተ ፡ መሥዋዕተ ፡ ዘናቀርብ ፡ ለከ ፡ ቀድስ ፡ ከናፍሪነ ፡ ወአንጽሕ ፡ አልባቢነ ፡ እምተቶስሖ ፡ በከንቱ ። ወፈኑ ፡ ላዕሌነ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ንትአማኅ ፡ በበይናቲነ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ፡ ወንትመጦ ፡ እምሀብትከ ፡ ሰማያዊት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እንበለ ፡ሞት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፻፲፰ ፤ ዘቦቱ ፡ ለከ ፡ ምስሌሁ ፡ ወምስለ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ማኅየዊ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌከ ስብሐት ፡ ወእኂዝ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፻፲፩ ፡ ሥጋውያን ፡ የምንሆን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ የሥጋን ፡ ሕግ ፡ እናስባለን ፤ የሥጋንም ፡ ሥራ ፡ እንሠራለን ፤ በሥጋ ፡ መንገድም ፡ እንሄዳለን ፡ አንተ ፡ ግን ፡ የመንፈስን ፡ ሥራ አስተምረን ፤ የመንፈስንም ፡ ሕግ ፡ አንተ ፡ አስረዳን ፡ የመንፈስን ፡ መንገድ ፡ ምራን ።

፻፲፪ ፤ እኛን ፡ ኃጥኣንን ፡ ብትምረን ፡ ያን ጊዜ ፡ መሐሪ ፡ ትባላለህና ፡ ጻድቃንን ፡ ግን ፡ ከሥራቸው ፡ የተነሣ ፡ ትምራቸዋለህ ፤ እንደ ፡ ጽድቃቸውም ፡ ትሰጣቸዋለህ ።

፻፲፫ ፡ የቀደመ ፡ በደላችንን ፡ አታስብብን ፤ አቤቱ ፡ ይቅርታህ ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረግልን ።

፻፲፬ ፤ ወደ ፡ አንተ ፡ እንጮሃለን ፤ ወደ ፡ አንተ ፡ እናለቅሳለን ፤ ወደ ፡ አንተ ፡ እንማለላለን ፡ ለዘላለሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

፻፲፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አንብሮ ፡ እድ ።

ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ልዑል ፡ ነው ፡ አለቃችን ፡ ሆይ ፡ የስጦታህን ፡ ብዛት ፡ መተርጐም ፡ የሚችል ፡ ልቡናና ፡ ኅሊና ፡ የለም ። እሊህን ፡ ከጥበበኞችና ፡ ከዐዋቆች ፡ ሠውረህ ፡ ለንዑሳን ፡ ሕፃናት ፡ ገልጸልሃና ።

፻፲፮ ፤ ነቢያትና ፡ ነገሥታት ፡ ያዩዋቸው ፡ ዘንድ ፡ የወደድዋቸውን ፡ ያላዩዋቸውንም እነርሱን ፡ ለእኛ ፡ ለኃጥኣን ፡ ሰጠህ ፡ እንገዛባቸው ፡ እንከብርባቸውም ፡ ዘንድ ፡ በአንድ ፡ ልጅህ ፡ ሥርዓት ፡ ባደረግህልን ፡ ጊዜ ፤ ይኸውም ፡ ኅቡእ ፡ ምሥጢር ፡ የብሉይ ፡ ሕግ ፡ ደም ፡ የሥጋ ፡ ጽድቅም ፡ ቢሆን ፡ የማያከብረው ፡ ነው ። ሰማያዊ ፡ በግዕና ፡ ያለ ፡ ሥጋ ፡ ነባቢ ፡ የሆነ ፡ መሥዋዕትም ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፻፲፯ ፤ ይህን ፡ መሥዋዕት ፡ የምናቀርብልህን ፡ የእኛን ፡ ከንፈሮች ፡ ቀድስ ፤ ልቡናችንንም ፡ በከንቱ ፡ ከመጨመር ፡ አንጻ ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ሀብት ፡ ወደእኛ ፡ ላክ ፤ በተለየች ፡ እማኄ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ እማኄን ፡ እናደርግ ፤ ዘንድ ፡ ሞት ፡ ከሌለባት ከሰማያዊት ፡ ሀብትህም ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፻፲፰ ፤ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ በአንተ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ጽንዕ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፤ ትክክልና ፡ ማኅየዊ ፡ ከሆነ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ ለአንተ ፡ ይገባል ። ዛሬም ፡ ዘወትርም ለዘላለሙ ፡ አሜን ።